# ጥር 14 ቀን 2015 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል የተፈጸመውን ሕገ ወጥ ሹመት ተከትሎ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ላይ የደረሱ ጉዳቶችን የሚያሳይ ልዩ ዘገባ

**ዓለማቀፍ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ጥምረት/International Orthodox Tewahedo Alliance - IOTA**

ጥር 2016 ዓ/ም

## ዓለማቀፍ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ጥምረት (International Orthodox Tewahedo Alliance - IOTA)

ዓለማ አቀፍ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ጥምረት መቀመጫውን በአሜሪካ ያደረገ ለትርፍ ያልተቋቋመ ተቋም ሲሆን በዋናንነት በዓለማችን ባሉ ኦርቶዶክሳውያን ላይ የሚደረሰውን ጥቃት ለዓለማቀፉ ማኅበረሰብ እንዲደርስ ይሰራል።

በ2015 ዓ/ም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ላይ ላለፉት 30 ዓመታት የደረሱ ጥቃቶችንና ያስከተሉትን ጉዳት የሚያሳይ ሪፖርት (https://iotaethio.org/wp-content/uploads/2023/07/Report_2023_IOTA.pdf) አዘጋጅቶ ያወጣ ሲሆን በዚህ ልዩ እትሙ ደግሞ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በወጡ ሶስት ሊቃነ ጳጳሳት መሪነት ጥር 14 ቀን 2015 ዓ/ም ከተፈጸመው ሕገ ወጥ ሹመት ጋር ተያይዞ የደረሱ ጉዳቶችን የሚያሳይ ሪፖርት አዘጋጅቶ በዚህ እትሙ ለአንባብያን አቅርቧል።

**ለተጨማሪ መረጃ**

Web site: https://iotaethio.org/
Email: office@iotaethio.org
Tweeter/X: https://twitter.com/iota_ethio
Facebook: https://www.facebook.com/profile.php?id=100067419963478

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ከሚባሉ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀስ ሲሆን ባሏት የምእመናን ቁጥር በዓለማችን በሁለተኛነት ደረጃ ላይ የምትገኝና በኢትዮጵያ ከ50 ሚልዮን በላይ ተከታዮች ያሏት አንጋፋ ቤተ ክርስቲያን ናት። ይች ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ዘመናት በአይነታቸም ይሁን በይዘታቸው የተለያዩ ፈተናዎች ያጋጠሟት ቢሆንም በእግዚአብሔር ቸርነትና በምእመናኑ ጥንካሬ የተጋረጡባትን ፈተናዎች ተሻግራ ከዚህ ዘመን ለመድረስ በቅታለች።

ቤተ ክርስቲያኗ በዕድሜ አንጋፋ ብትሆንም የራሷ ሊቃውንትን በመምረጥ ጳጳሳትን መሾም ከጀመረች ግን ገና የመቶ ዓመት ዕድሜኔን እንኳን አላስቆጠረችም። ከ1600 ዓመታት በላይ ከእስክንድርያ ተሹመው የሚላኩላትን ጳጳስት እንደራሷ አድርጋ ተቀብላ ስትመራ ቆይታለች። ለመጀመሪያ ጊዜ በ1928 ዓ/ም ከራሷ ሊቃወንት መካከል 5 መነኮሳትን መርጣ ወደ እስክንድርያ በመላክ ኤጵስ ቆጶሳት እንዲሾሙ ያደረገች ሲሆን በጥር 6 ቀን 1943 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ባስልዮስን የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ተብለው ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ካይሮ ላይ በግብጹ አቡነ ዮሳብ ሁለተኛ ተሰየሙ። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም ከ1951 ዓ.ም ከሊቀ ጵጵስና ወደ ፓትርያርክነት መንበር ከፍ ያለች ሲሆን ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው ፓትርያርክ ሆኑ። በዚህም ሁኔታ ራሷን ማስተዳደር ከቻለች በኋላ የጳጳሳት ሹመት አስፈላጊ ሲሆን በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት ጳጳስትን እየሾመች ትገኛለች። ባለፉት 50 ዓመታት የቅዱስ ሲኖዶስ ታሪክ በአጠቃላይ 6 ፓትርያሪክ የሾመች ሲሆን በእነሱና በቅዱስ ሲኖዶሱ ወሳኔ መሠረት በሀገር ውስጥና በወጩ ዓለም ተዘዋውረው ቤተ ክርስቲያኗን የሚመሩ ብዛት ያላቸው ኤጲስ ኦቆጶሳትን ለመሾም ችላለች።

አጭር በሚባለው የቅዱስ ሲኖዶስ ዕድሜ ቤተ ክርስቲያኗ አንድነቷን የሚፈታተኑ ብዙ ፈተናዎች የገጠሟት ቢሆንም ከደርግ መንግሥት መውደቅና የኢህአደግ መንግሥት ወደ ሥልጣን መምጣት ጋር ተያይዞ በወቅቱ የነበሩት ፓትርያሪክ አቡነ መርቆሬዎስ ተሰደው ወደ አሜሪካ እንዲወጡ የተደረገበትና "ስደተኛ" በሚል ሁለተኛ ሲኖዶስ በመመሥረት ምእመናንን ለመለያየትና ቤተ ክስርቲያንን ለአደጋ እንድትጋለጥ አድርጓት እንደነበር ይታወቃል። ይህ መለያየት በብፁዓን አባቶችና በቤተ ክስርቲያኗ ቅን አገልጋዮች ጥረት እንዲሁም በመንግሥት ድጋፍ በእርቅ እንዲቋጭና የአባቶችና የምእመናን አንድነት እንዲመጣ መደረጉ ለቤተ ክስርቲያኗ አንድነት ትልቅ አስተዋጾ አድርጓል።

ይሁን እንጂ ይህ አንድነት ብዙም ሳይቆይ ቤተ ክስርቲያኗን ለሌላ መለያየት የሚዳርግና በተለይም ምእመናን በጎሳ የሚከፋፍል ኢቀኖናዊ የሆነ ሕገወጥ ሹመት ከኦሮምያ ክልል ተወላጅ ነን በሚሉ ሦስት ሊቃነ ጳጳሳት መሪነት በጥር 14 ቀን 2015 ዓ/ም ተከናውኗል። የዚህ ሪፖርት አጠቃላይ ይዘትም ከዚህ ሕገ ወጥ ሹመት ጋር ተያይዞ በአብያተ ክስርቲያናት፣ አገልጋይ ካህናትና ምእመናን ላይ የደረሱ አደጋዎችን የሚዳስስ ይሆናል።

## የዘገባው ዋና ዓላማ

ይህ ዘገባ በዋናነት በጥር 14 ቀን 2015 ዓ/ም ከተከናወነው ሕገ ወጥ የኤጲስ ቆጶሳት ሹመት ጋር ተያይዞ በሀገሪቱ ባሉ አብያተ ክስርቲያናት፣ ካህናትና ምእመናን ላይ የደረሰውን ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት ማሳየት ነው።

## የችግሩ መነሻ

በጥር 14 2015 ዓ.ም በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት በሶዶ ዳጬ ወረዳ ከወሊሶ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ ሐሮ ደብረ ጽጌ ቅዱስ በዓለ ወልድ እና ቅዱስ ዑራኤል ገዳም "የኤጲስ ቆጶሳት ሲመት" የተሰኘው የቤተክርስቲያን ቀኖና ያልተከተለ ድርጊት ተፈጽሟል። ይህም ሕገ ወጥ ሹመት የቅዱስ ሲኖዶስ አባል በሆኑ 3 ሊቃነ ጳጳሳት ማለትም በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ በወቅቱ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤ ብጹዕ አቡነ ኤዎስጣጤዎስ በወቅቱ በአሜሪካ የሚኒሶታና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና ብጹዕ አቡነ ዜና ማርቆስ በወቅቱ የጉጂ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩ ሲሆን በ3ቱ ጳጳሳት መሪነት የተደረገ የ26 ሕገ ወጥ የኤጲስ ቆጶሳት ሲመት ነው።

በአካባቢው የነበሩ የዐይን እማኞች እንደገለጹት ከሆነ ሹመቱ ከመደረጉ አስቀድመው በነበሩት ቀናት ወደ ገዳሙ የኦሮሚያ ልዩ ኃይል ልብስ የለበሱ ታጣቂዎች ተልከው አካባቢውን የማጽዳት ሥራ እንዲሠራ ተደርጓል። የጥምቀት ዕለት ማታ የገዳሙን አበምኔት አባ ወልደ ሰንበት አፍነው ወዳልታወቀ ቦታ ወሰደዋቸው የነበረ ሲሆን ጥር 13 ቀን 2015 ዓ.ም ወደ ገዳሙ መልሰዋቸዋል። በገዳሙ ሰፍረው የነበሩት ታጣቂዎችም ጉዳዩን ሊቃወሙ ይችላሉ ተብለው የሚያስቧቸውን አገልጋዮች ሹመቱ ከመፈጸሙ ከሦስት ቀናት በፊት ማለትም ጥር 12 ቀን 2015 ዓ/ም ከገዳሙ እንዲወጡ የተደረገ ሲሆን ከዚያን ዕለት ጀምሮ ወደ ገዳሙ አካባቢ ማንም ዝር እንዳይል በታጣቂዎች ጥበቃ ይደረግ ነበር።

ሿሚዎችና ተሿሚዎች ወደ ገዳሙ የገቡት በተበታተነ መንገድ ከጥር 13 ቀን 2015 ዓ.ም ከሰዓት ጀምሮ እንደነበረም በአካባቢው የነበሩ የዐይን እማኞቹ ይገልጻሉ። የቅዳሴ ሥርዓቱ የተከናወነው ከሌላ ቦታ ይዘዋቸው በመጡ ልኡካን ነው። አስቀድሞ ይህ ቦታ ታስቦ የነበረው ለማረፊያነት እንጂ ለሹመት አልነበረም። ተሿሚዎቹ ከዚህ ገዳም ቆይተው ጥር 17 ወይም ጥር 21 ቀን 2015 ዓ.ም ደብረ ሊባኖስ፣ ቁልቢ ወይም አዳዲ ማርያም ገዳም ይፈጸማል ተብሎ የታሰበ ቢሆንም ጉዳዩን በሚመሩት የክልሉ አካላት የአሳብ ለውጥ ተደርጎ ሹመቱ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሶዶ ዳጪ ወረዳ ሀሮ ደብረ ጽጌ ቅዱስ በዓለ ወልድ እና ቅዱስ ዑራኤል ገዳም እንዲሆን ቀኑም ቀደም ብሎ ጥር 14 እንዲፈጸም ተደርጓል። ወደ አዲስ አበባ ሲመጡም ሆነ ሹመቱ ወደተፈጸመበት ቦታ ሲሔዱ ለምን ዓላማ እንደሚሔዱ የማያውቁ (ሹመቱ በዚያን ቀን መሆኑ ያልተነገራቸው) ተሿሚዎች እንደነበሩም በወቅቱ የነበሩ እማኞቹ ገልጸዋል። ከተሿሚዎቹ ውስጥም ሹመቱ በዕለቱ እንደሚፈጸም ቀድመው ሳያሳውቁኝና ሳያማክሩኝ ነው የፈጸሙት የሚል ቅሬታ ያላቸው እንደነበሩ ታውቋል። ከዚህም የምንረዳው አጠቃላይ የሹመት ሒደቱ ይመራ የነበረው በሦስቱ ጳጳሳት ብቻ ሳይሆን በኦሮሚያ ክልል የጸጥታ መዋቅር እንደነበረ ነው።

በዚህ አግባብ ሕገ ወጥ ሹመቱ ጥር 14 ቀን 2015 ዓ.ም ከተፈጸመ በኋላ በዕለቱም ከሰዓት በኋላ ሲመቱን የመሩት ሦስቱ ሊቃነ ጳጳሳት እና ተሿሚዎች ሹመቱ ከተፈጸመበት ደቡብ ምዕራብ ሸዋ በክልሉ የጸጥታ ኀይል ጥበቃ እየተደረገላቸው ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡና በተዘጋጀላቸው ማረፊያ እንዲያርፉ ተደርጓል ። ከዚያም አስቀድሞ ተዘጋጅቶላቸው በነበረው አዲስ አበባ ኮተቤ አከባቢ በሚገኘው ክራዎን ሆቴል ውስጥ 26 "ኤጲስ ቆጶሳት" እንደሾሙ እና በ24 አህጉረ ስብከት እና በሁለት

ገዳማት ላይ በበላይ ጠባቂነት እንደመደቡ መግለጫ ሰጡ [1]። መተሰጠው መግለጫ መሠረት በዕለቱ ሹመት ተሰጣቸው የተባሉ መነኮሳት ዝርዝር እንደሚከተለው ነው።

ሰንጠረዥ 1፡ ሹመት ተሰጣቸው የተባሉ መነኮሳት ዝርዝር

| **የቀድሞ ስም** | **በሕገወጥ የተሰጠ የጵጵስና ስም** | **የተመደቡበት ሀ/ስብከት** | **አሁን ያሉበት ሁኔታ** |
|---|---|---|---|
| አባ ገ/ማርያም ነጋሳ | አቡነ ገብርኤል | ምዕራብ ወለጋ | በሕገወጥ የተሾሙና ያለተመለሱ |
| አባ ተ/ሃይማኖት ወልዱ | አቡነ ባስልዮስ | ድሬዳዋ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ገብርኤል ወ/ዮሐንስ | አቡነ ጢሞቴዎስ | ጉራጌ ሶዶ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ገ/እግዚአብሔር ታደለ | አቡነ ጳውሎስ | ምዕራብ አርሲ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ሚካኤል ገ/ማርያም | አቡነ ኤልሳዕ | ከምባታ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ኃይሉ እንዳለ | አቡነ ገሪማ | ምሥራቅ ሐረርጌ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ተ/ማርያም ስሜ | አቡነ ተ/ሃይማኖት | ጉጂ ሊበን | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ኃ/ኢየሱስ መንግስቱ | አቡነ ዕዝራ | ከፋ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ወ/ኢየሱስ ኢፋ | አቡነ ኢያሱ | ቄለም ወለጋ | በሕገወጥ የተሾሙና ያለተመለሱ |
| አባ ጳውሎስ ከበደ | አቡነ ዳንኤል | ሀዲያ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ኃ/ኢየሱስ ተስፋዬ | አቡነ በርሱማ | ምሥራቅ ወለጋ | በሕገወጥ የተሾሙና ያለተመለሱ |
| አባ ገ/ኢየሱስ ገለታ | አቡነ ሚናስ | ሆሮ ጉዱሩ | በሕገወጥ የተሾሙና ያለተመለሱ |
| አባ ጸጋዘአብ አዱኛ | አቡነ ኤጲፋንዮስ | ምሁር ገዳም የበላይ ኃላፊ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ኃ/ማርያም ጌታቸው | አቡነ አቤል | ምዕራብ ሐረርጌ | በይቅርታ የተመለሱና በቅዱስ ሲኖዶስ እንደ አዲስ የተሾሙ |
| አባ ወ/ጊዮርጊስ ኃ/ሚካኤል | አቡነ በርተሎሚዎስ | ከሚሴ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ እስጢፋኖስ ገብሬ | አቡነ ራጉኤል | ባሌ ረዳት ጳጳስ | በይቅርታ የተመለሱ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| አባ ገ/መድኅን ገ/ማርያም | አቡነ ዑራኤል | ጎፋ ባስኬቶ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ኃ/ሚካኤል ንጉሤ | አቡነ አኖሬዎስ | ጊኒር | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ አብርሃም መስቀሌ | አቡነ ኒቆዲሞስ | ዳውሮ፣ ኮንታ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ንዋየ ሥላሴ አክሊሉ | አቡነ ሀ/ማርያም | ምዕራብ ጉጂ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ኪ/ማርያም ቶሎሳ | አቡነ ተ/ሃዋርያት | ጅማና የም | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ወ/ማርያም ጸጋ | አቡነ አብሳዲ | ቦረና | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ አምደሚካኤል ኃይሌ | አቡነ መርቆሬዎስ | አርሲ | በይቅርታ የተመለሱና በቅዱስ ሲኖዶስ እንደ አዲስ የተሾሙ |
| አባ መርሐጽድቅ ኃ/ማርያም | አቡነ ደቅስዮስ | ጌዴኦ፣ቡርጂ፣አማሮ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ሞገስ ኃ/ማርያም | አቡነ ኤፍሬም | መናገሻ ጋራ መድኃኒዓለምና፤ ደ/ፅሐይ ቅ/ጊዮርጊስ የበላይ ኃላፊ | በይቅርታ የተመለሱ |
| አባ ገ/ኢየሱስ ንጉሤ | አቡነ አልዓዛር | ቡኖ በደሌ | በይቅርታ የተመለሱ |

በሕገወጥ መንገድ ራሱን የሾመው ስብስብም የኦሮሚያና የብሔር ብሔረሰቦች ሲኖዶስ ሲል ራሱን ሰይሟል። በዚህ መግለጫ ለመሾማቸው ምክንያት አድርገው ያቀረቡት የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ሲኖዶስ "አባቶችን ከተለያዩ አካባቢዎች ከማፍራት ይልቅ ከአንድ ወገን ብቻ በመሾም ለኦሮሚያ፣ ደቡብ ምሥራቅ፣ ደቡብ ምዕራብና ውጪ ሀገራት መላካቸው፣ በኦሮሚያና መሰል አህጉረ ስብከት የሕዝቡን ባህልና ቋንቋ የማያውቁ አባቶች መመደባቸው፣ ኦሮሚያን እንደ አንድ ሀገረ ስብከት መመልከትና ጨፍልቆ ለማስተዳደር መሞከር፣ በሰሜኑ ክፍል ረዳት ሊቃነ ጳጳሳት ሲመደቡ በኦሮሚያና ደቡብ ግን ብዙ አህጉረ ስብከትን በአንድ ሊቀ ጳጳስ እንዲመሩ መደረጉ ፤ አሁን በሥራ ላይ ያለው ቅዱስ ሲኖዶስ ከ85 መቶ በላይ ከአንድ ወገን ተዋቅሮ የሚገኝ መሆኑ" የሚሉ ሲሆኑ በዚህም ሁሉን አቀፍ ሲኖዶስ ነው ብሎ መቀበል ባለመቻሉ ሁሉንም የሀገሪቱን ሕዝቦች ያቀፈ ሲኖዶስ ዛሬ አቋቁመን በይፋ ሥራ መጀመራቸውን ገልተዋል። እነዚህ አባቶች ቅዱስ ሲኖዶስ በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ የቤተ ክርስቲያን አካል መሆኑን እንደማይቀበሉ ገልጸዋል።



*ምስል 1፡ በሕገ ወጡ ሹመት የተሳተፉ ሊቃነ ጳጳሳትና ተሿሚዎቹ 26 መነኮሳት*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በጥር 15 ቀን 2015 ዓ/ም ድርጊት አስመልክቶ በሰጠው መግለጫ በሀገር ውስጥ እና ውጪ ያሉ ሊቃነ ጳጳሳት በአስቸኳይ ወደ መንበረ ፓትሪያርክ እንዲመጡ ፤መንግሥት ክስተቱ በሀገር ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ተመልክቶ በጉዳዩ ላይ ሕጋዊ ኀላፊነቱን እንዲወጣ ፤ምእምናን ቤተክርስቲያንን ከመቸውም በላይ በንቃት ፣በሐሳብና በጸሎት እንዲጠብቁ መግለጫን አስተላልፏል [2]። ይህን ተከትሎ የተለያዩ የቤተክርስቲያኒቱ መዋቅር ውስጥ የሚገኙ አካላት በጉዳዩ ዙሪያ ያላቸውን ምልከታና አቋማቸውን ገልጸዋል።

በቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት የተሰጠውን መግለጫ ተከትሎ በተመሳሳይ ቀን የጠቅላይ ቤተክህነት አስተዳደር ጉባኤ ሃይማኖታዊ ክህደት ፣ቀኖናዊ ጥሰት እና አስተዳደራዊ ግድፈት የታየበትን የወሊሶውን ሲመት ያወገዘ ሲሆን [3] ፤የመንበረ ፓትሪያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በአዲስ አበባ የሚገኘውን በዚህ ድርጊት ውስጥ የመሪነት ድርሻ ተጫውተዋል ያላቸውን 3 ሊቃነ ጳጳሳት (አቡነ ሳዊሮስ፣አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ፣አቡነ ዜናማርቆስ) ማረፊያ ቤት አሽጓል። እንዲሁም ከ26 ተሿሚዎች መካከል ለሆኑት ሊቀ ጉባኤ ተክለሃይማኖት ወልዱ የሰጠውን የመኖሪያ ቤት ውል አቋረጦ ቤቱንም አሽጓል። በተለያዩ የቤተክርስቲያን መዋቅር ውስጥ ያሉ አካላት አቋም ከጉዳዮ ጋር ተያይዞ የአቋም መግለጫ በማውጣት ድርጊቱን አውግዘዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጥር 18 ቀን 2015 ዓ/ም ባደረገው አስቸኳይ ጉባኤ ስለተፈጸመው የቀኖና ጥሰትና ሕገ ወጥ ሹመት ከተወያየ በኋላ "በአጠቃላይ የተፈጸመው ሕገ ወጥ ተግባር በሕገ ሰብእም ሆነ በሕገ እግዚአብሔር ሚዛን የተወገዘ ከመሠረተ እምነት የተለየ፣ በአበው ቀኖና፣ በሕገ ቤተ ክርስቲያን እና በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በአጠቃላይ ተቀባይት የሌለው ነው " በማለት በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 138 መሠረት ጥር 14 ቀን 2015 ዓ.ም በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት በሶዶ ዳጬ ወረዳ ሐሮ ባለወልድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ 1ኛ) አባ ሳዊሮስ 2ኛ) አባ ኤዎስጣቴዎስ

3ኛ) አባ ዜና ማርቆስ የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና በመጣስ ባልተሰጣቸው ሥልጣን 26 ኤጲስ ቆጶሳትን ሾመናል፤ ሲኖዶስ አቋቁመናል በማለት በማኅበራዊ እና በብሮድካስት ሚዲያዎች በሰጡት መግለጫ የተረጋገጠ በመሆኑ በዚሁ ድርጊታቸው በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም የሚኖረውን ሕዝበ ክርስቲያንን በማታለል የክህደት እና የኑፋቄ ተግባር በመፈጸማቸው በመንፈስ ቅዱስ የሚመራው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ፤ ከቤተ ክርስቲያን የተሰጣቸውን ከዲቁና ጀምሮ ያለው ሙሉ ሥልጣነ ክህነት በመሻር አውግዞ ለይቷቸዋል በማለት ውሳኔ አሳልፏል ።

በተጨማሪም የቅዱስ ሲኖዶሱንና የቤተ ክርስቲያኒቱን ልዕልና በመዳፈር እና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በመጣስ በተነሳሱ ግለሰቦች አማካኝነት የኤጲስ ቆጶስነት ሹመት አግኝተናል፤ ተሾመናል እያሉ የሚገኙ 25 መነኰሳት በሕገ ወጥ መንገድ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንንን ጥሰው የተገኙ በመሆኑ አስቀድሞ ከቤተ ክርስቲያን የተሰጣቸው ከዲቁና ጀምሮ ያለው ሙሉ ሥልጣነ ክህነት ተሽሮ ከጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዐተ ጉባኤ ተወግዘው ከቤተ ክርስቲያን እንዲለዩ ውሳኔ አሳልፏል [4] ።

ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ የተፈጸመውን ሕገወጥ ሲመት በመቃወም አኀት አብያተ ክርስቲያናት፤ በሀገር ውስጥና በወጭ የሚገኙ አህጉረ ስብከቶች፤ በቤተ ክስርቲያኗ ስር የሚገኙ መንፈሳዊ ማኅበራት፣ የሲቪክና የፖለቲካ ድርጅቶች መግለጫ አውጥተዋል። በተለይም የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፤ የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፣ የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፣ ከምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መካከል የሆነችው የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን [5] እና የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን [6] የተፈጸመውን ሕገወጥ ሲመት ሕገ ቤተክርስቲያንን ያልተከተለ በመሆኑ የማይቀበሉት እንደሆነና ከቅዱስ ሲኖዶስ ጎን እንደሚቆሙ በመገለጫቸው አጽንዖት በመስጠት ገልጸዋል። ጉዳዩን አስመልክተው መግለጫ ከሰጡ የሰብአዊ መብት እና ሲቪክ ማኅበረሰብ ተቋማት መካከል የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ [7]፣ ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኀን ባለሙያዎች ማኅበር [8]፣ የኢትዮጵያውያን አሜሪካን ሲቪክ ካውንስልና የኢትዮጵያውያን አሜሪካን ደቨሎፕመንት ካውንስል ተጠቃሽ ናቸው [9]። በተጨማሪም ኢሕአፓ፣ መኢአድ ፓርቲ፣ እናት ፓርቲ እና ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ሕገ ወጥ ሹመቱን በማስመልከት አጋርነታቸውን በማሳየት መገለጫ አውጥተዋል[10]።

## መረጃ የተሰበሰበበት መንገድ

*መረጃው የዚህ ሪፖርት አዘጋጅ የሆነው ክፍል በሀገሪቱ ካሉ የመረጃ ሠራተኞች ጋር በመሆን የነበሩትን እንቅስቃሴዎች በማስረጃ አስደግፎ ሲሰበስብ የነበረ ሲሆን ለሪፖርቱ ዝግጅት በመረጃ ሰዎች የተሰበሰቡ ማስረጃዎችን እንደዋና የመረጃ ምንጭ ተጠቅሟል። በተጨማሪም ችግሩ ከተፈጠረ በኋላ በነበሩ ሳምንታት መጠይቆችን በመላክ ችግሩ በተፈጠረባቸው አካባቢዎች ከሚኖሩ ከተመረጡ ገለሰቦች መረጃ አሰባስቧል። በተጨማሪም በወቅቱ በቅዱስ ሲኖዶስና በመንግሥት አካላት የወጡ መግለጫዎችን እንደማገናዘቢያና እንደ ሁለተኛ የመረጃ ምንጭ የተጠቀመ ሲሆን ተአማኒ ከሆኑ የቤተ ክስርቲያኗና የመንግት የዜና አውታሮች ያሰራጫቸውንም መረጃዎች እንደግብዓት ውለዋል። መረጃዎቹ ተአማኒነታቸውን ለማረጋገጥ የተሰበሰቡ መረጃውን በመጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር የማገናዘብ ሥራ በጥንቃቄ ለመሥራት ተሞክሯል።*

## ጉዳት ያስተናገዱ አካባቢዎች

ከተፈጠረው ሕገወጥ ሹመት ጋር በተያያዘ የሕገወጡን ሹመት በሚቀበሉ ግለሰቦችና መንግሥታዊ ድጋፍ በሚሰጧቸው የመንግሥት የጸጥታ አካላት አማካኝነት የቤተ ክስርቲያኗን ሕጋዊ መብት ለማስከበር በሞከሩ አገልጋዮችና ምእመናን ላይ ምንም ሕጋዊ መሠረት የሌለው ግድያ፤ ከፍተኛ የሆነ ድብደባ፣ እስርና ከሥራ የማፈናቀል ተግባር ተከናውኗል። ይህ ተግባር

የተፈጸመባቸው አካባቢዎች በአብዛሃኛው በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ዋና ዋና የሚባሉት አካባቢዎች ከዚህ በታች በተቀመጠው ካርታ ላይ የሚታዩ ናቸው።




*ምስል 2፡ ጥር 14 2015 ዓ/ም ከተፈጸመው ሕገ ወጥ ሹመት ጋር ተያይዞ ጉዳት ያስተናገዱ አካባቢዎች*

# የደረሱ ጉዳቶች

## 1. ከዳኝነት ውጭ የተፈጸሙ ግድያዎች

### 1.1. ሻሸመኔ

ከሕገ ወጥ ሹመቱ ጋር ተያይዞ ቅዱስ ሲኖዶስ የሰጠውን መመሪያ በማክበር በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን በመገኘት ቤተ ክስርቲያናቸውን ሲጠብቁ ከነበሩ ምእመናን መካከል ጥር 27/2015 ዓ.ም ከመንግስት የጸጥታ አካላት በተተኮሰ ጥይትና ሕገወጡ ቡድን ባደራጃቸው ግለሰቦች ድብደባ ከ30 በላይ ምእመናን የተገደሉ ሲሆን አብዛኛዎቹ በዚያው በሻሸመኔ ባሉ አብያተ

ክርስቲያናት ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጥሟል። የተወሰኑት ወደ ትውልድ ሀገራቸው እንዲላኩ ተደርጓል። በእለቱ የተገደሉ ምእመናን ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል።

### ሰንጠረዥ 2፡ ጥር 27/2015 ዓ.ም ከመንግሥት የጽጥታ አካላት በተተኮሰ ጥይትና ሕገወጡ ቡድን ባደራጃቸው ግለሰቦች ድብደባ የተገደሉ አገልጋዮችና ምእመናን

| የተጎጂ ስም | ዕድሜ | የጉዳት አይነት | በቤተሰብ ያለው ኀላፊነት | አድራሻ | የአገልግሎት ድርሻ | የተቀበረበት ደብር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ዘሪሁን ቱጂ | 26 | ሞት | ተመራቂ ተማሪ | ሻ/ኔ 08 ቀበሌ | ቅ/ሚካኤል ሰ/ት ቤተ አባል | ሻ/ኔ አቡነ ተ/ይማኖት |
| አየለ ማንደፍሮ | 30 | ሞት | ተመራቂ ተማሪ | ሻ/ኔ 08 ቀበሌ | ቅ/ሚካኤል ሰ/ት ቤተ አባል | ሻ/ኔ አቡነ ተ/ይማኖት |
| ዲ/ን አዲሱ በቀለ | 24 | ሞት | ተማሪ | ሻ/ኔ 08 ቀበሌ | ሻ/ኔ ደብረ ስ/ቅ/ሚካኤል አገልጋይ | ሻ/ኔ አቡነ ተ/ይማኖት |
| ፍቃዱ ደጉ | 19 | ሞት | ተማሪ እና እናተኑን በቀን ሥራ የሚያስተዳድር | ሻ/ኔ 08 ቀበሌ | የማህበረ ቅዱሳን የበገና ዘማሪ | ሻ/ኔ አቡነ ተ/ይማኖት |
| አለማየሁ ወልዴ | | ሞት | በግል ሥራ የሚቀሳቀስ | ሻ/ኔ 08 ቀበሌ | ሻ/ኔ ደብረ ስ/ቅ/ሚካኤል አገልጋይ | ሻ/ኔ አቡነ ተ/ይማኖት |
| ቀሲስ ሀረገወይን | 38 | ሞት | የቤተሰብ መሪ | ሻ/ኔ 02 ቀበሌ | ሻ/ኔ ደብረ ስ/ቅ/ሚካኤል ቀዳሽ | ሻ/ኔ አቡነ ተ/ይማኖት |
| አያሌዉ ተፈራ | 38 | ሞት | የቤሰብ መሪ | ሻ/ኔ 02 ቀበሌ | ምዕመን | ሻ/ኔ አቡነ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ተ/ይማኖት |
| ምትኩ አንቺቤ | 40 | ሞት | ቤሰሰብ አስተደዳሪ | ሻ/ኔ 08 ቀበሌ | ምዕመን | ሻ/ኔ አቡነ ተ/ይማኖት |
| ገመቹ ጉዲና | 32 | ሞት | በግል ተዳዳሪ | ሻ/ኔ 08 ቀበሌ | ልደታ ሰ/ት አገልጋይ | ሻ/ኔ አቡነ ተ/ይማኖት |
| አሸናፊ ሙሉዬ | 49 | ሞት | የ 7ቤተሰብ መሪ | ሻ/ኔ 08 ቀበሌ | ምዕመን | ጉራጌ ቡኢ ቀጨኔ መድኃኒያለም |
| አስቻለዉ በረጋ | 35 | ሞት | የቤተሰብ አስተዳዳሪ | ሻ/ኔ 08 ቀበሌ | ምዕመን | ሻ/ኔ አቡነ ተ/ይማኖት |
| አዳነ ግርማ | 26 | ሞት | ተማሪ | ሻ/ኔ 08 ቀበሌ | ልደታ ሰ/ት/ቤት አገልጋይ | ሻ/ኔ አቡነ ተ/ይማኖት |
| ግርማ አለማየሁ | 24 | ሞት | ተማሪ | ጊንዲር | ሻ/ኔ አቡነ ተ/ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት አገልጋይ | ጊንዲር ቅ/ሚካኤል |
| ለጊዜው ስሟ ያልታውቀች | | ሞት | ተማሪ | ለት/ት መጣ አድራሻዋ ያልታወቀ | | ሻ/ኔ አቡነ ተ/ይማኖት |




*ምስል 3፡ በሻሸመኔ ጥር 27/2015 ዓ.ም ከመንግስት የጸጥታ አካላት በተተኮሰ ጥይትና ሕገወጡ ቡድን ባደራጃቸው ግለሰቦች ተደብድበው የተገደሉ ምእመናን የፍታት ጸሎት*

### 1.2. ወለቴ

ወለቴ ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ አነስተኛ ከተማ ሲሆን የካቲት 02/2015 ዓ.ም በከተማው በሚገኝ የቅዱስ ዮሐንስ ቤ/ክ በተሰባሰቡ ምእመናን ላይ የመንገስት ወታደሮች ባደረሱት ጥቃትና በተተኮሰ ጥይት ወጣት ዳዊት ክንፈ የተባለ ምእመና በአሰቃቂ ሁኔታ ተገሏል።

## 2. የአካል መጉደል

ምዕራብ አርሲ ሀገረ ስብከት፣ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት፣ ምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት፣ ምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት የአካል ጉዳት የተመዘገበባቸው አህጉረ ስብከት ናቸው። ምዕራብ አርሲ ሀገረ ስብከት በጸጥታ አካላት እና ከእነርሱ ጋር በተባበሩ ሰዎች በተፈጸመ ጥቃት በጥይት ተመትተውና በዱላ ተደብድበውና ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው 393 ምእመናን ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ 134 ቀላል፣ 214 መካከለኛ ቀሪዎቹ 45 ምእመናን ከፍተኛ የሚባል አደጋ የደረሰባቸው ናቸው። ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት 55 እንዲሁም ምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት 53 ኦርቶዶክሳውያን በጸጥታ አካላት እና በአዲስ ተሿሚዎች ደጋፊዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል። ምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት አዲስ ተሿሚዎች ባደራጇቸው ቡድኖች ተደብድበው ጉዳት የደረሰባቸው 8 (ስምንት) አገልጋዮች ሲሆኑ በተለይም ዲ/ን ሀብታሙ ዴቢሳ የሚባል አገልጋይ ኩላሊቱ ላይ በደረሰበት ድብደባ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል። ለረጅም ጊዜም በሕክምና ላይ ይገኛል። ዲያቆን ዓለማየሁ ሰለሞን የነቀምት ርእሰ አድባራት ደብረ ጽ/ዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከሕገወጡ አካላት ጋር ባለመተባበሩ በከፍተኛ

ሁኔታ ደብድበው በሞትና በሕይወት መካከል ጥለውት ሔደው በሕክምና ሕይወቱ ሊተርፍ ችሏል። የካቲት 16 ቀን 2015 ዓ.ም የነቀምት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ፣ የካቲት 19 የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ በመደብደብ ቅዳሴ እንዲታጎል አድርገዋል። በተመሳሳይ ዕለት የካቲት 19 ቀን 2015 ዓ.ም ገነተ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ስብሰባ ላይ የነበሩ አገልጋዮች ላይ ባደራጇቸው ቡድኖች በፈጸሙት ድብደባ በጠቅላላው አምስት አገልጋዮች ተጎድተው ወደ ሕክምና እንደሔዱ ለማወቅ ተችሏል።

በተመሳሳይ ሁኔታ የካቲት 02/2015 ዓ.ም በወለቴ ቅዱስ ዮሐንስ ቤ/ክ በምዕመናን ላይ በደረሰው ጉዳት በአጣቃላይ 38 ምእመናን ላይ ጉዳት የደረሰ ሲሆን ከነዚህም ወስጥ 32 የዱላ ድብደባ መፈንከት፤ የእግርና የእጅ ስብራት የደረሰባቸው ሲሆን 5ቱ በአለርት ሆስፒታል፤ 13 በወለቴ ጤና ጣቢያና 9 በግል የሕክምና እገዛ እንዲያገኙ ተደርጓል። 6 ምእመናን ከጸጥታ አካላት በተተኮሰ ጥይት የተለያየ ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን ሁለቱ በአለርትና 4ቱ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታሎች እገዛ እንዲያገኙ ተደርጓል።

## 3. የዘፈቀደ እስር

ከሕገወጥ ሹመቱ ጋር ተያይዞ ቅዱስ ሲኖዶስ ያስተላለፈውን አዋጅና ወሳኔ ተግባራዊ እንዲሆን በተሰጣቸው ሃላፊነትና እንደምእመናን የቤተ ክርስቲያንን ጥሪ በሰላማዊ መንገድ ለመተግበር ሲሞክሩ የነበሩ ያልታጠቁ አገልጋይ ካህናትና ምእመናን ላይ የዘፈቀደ እስራት በተለያዩ የኦሮምያ ክልል ከተሞች ተፈጽሟል። ይህንንም በበላይነት ሲመሩ የነበሩ የኦሮሚያ ልዩ ሃይልና ፖሊስ ሲሆኑ በእስር ላይ በነበሩ ምእመናን ላይ ሕገወጥ ድብደባና እንግልት እንዳደረሱባቸው ከታሳሪ ቤተሰቦችና ታስረው ከነበሩ ግለሰቦች ለመረዳት ተችሏል። በእስር ላይ በነበሩ ግለሰቦች ላይ ይፈጸሙ ከነበሩ ኢሰብዓዊ ጥቃቶች መካከል 1) በጨለማ ቤት ማሰር 2) በጠባብ ክፍል ውስጥ ብዙ እስረኞችን ማጎር 3) በሰላማዊ መንገድ ድምጻቸውን በሚያሰሙ ምእመናንና ካህናት ላይ በዱላ መደብደብ ተጠቃሽ ሲሆኑ በተወሰኑት ታሳሪዎች ላይም መካከለኛና አነስተኛ ጉዳት ሊደርስ ችሏል። ከጥር  እስከ የካቲት በነበሩት ቀናት በዘፈቀደ ታስረው የነበሩ አገልጋዮችና ምእመናን ቁጥር በትክክል ለማገኘት አስቸጋሪ ቢሆንም ይህ ሪፖርት በሚዘጋጅበት ወቅት ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን በማመሳከር ለማቅረብ ተችሏል። ከዚህ በታች  በሰንጠረዥ የተቀመጠው መረጃ በሁለቱ ተከታታይ ወራት ታስረው የተፈቱና እስካሁንም በተለያየ ማጎሪያ ውስጥ የሚገኙ ምእመናንን ያካተተ ሲሆን ቁጥሩ ከተቀመጠው ሊበልጥ እንደሚችል ይገመታል።

ሰንጠረዥ 3፡ ታስረው የተፈቱና እስካሁንም በተለያየ ማጎሪያ ውስጥ የሚገኙ ምእመናንን

| የቦታ ስም | ዕድሜ | ወንድ | ሴት | ጠቅላላ | የታሰሩበት ቦታ | የአገልግሎት ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ጅማ** | | 9 | 1 | 10 | ወረዳ 1ና 2 ፖሊስ ጣቢያ | |
| **በደሌ** | | 7 | | 7 | በደሌ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ | የሀገረ ስብከቱ ፀሐፊ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **አዳማ** | | 64 | 20 | 84 | አዳማ ወረዳ 2፣4፣ 18 ፖሊስ ጣቢያና ፣ኬላ፣አሰላ መነኻሪያ፣ ቦኩ ፖሊስ ጣቢያ | የማኅበረ ቅዱሳን ፀሐፊና አባላት፣ የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች |
| **አሰላ** | | 10 | | 10 | | |
| **አምቦ** | | 3 | 7 | 10 | 02 ፖሊስ ጣቢያ | |
| **የሻኪሶ ወረዳ** | | 12 | 3 | 15 | | የያቤሎ ደብረ ፅዮንና እግዚአብሔር አብ ወአቡነሐራ ድንግል ቤ/ክ አስተዳዳሪ፣የሰ/ጉ አባላት |
| **ቦሬ ወረዳ** | | 2 | 4 | 6 | | |
| **አዶላ ወረዳ** | | 5 | 1 | 6 | | |
| **ሻምቡ ከተማ** | | 3 | | 3 | 01 ቀበሌ ፖሊስ ጣቢያ | የማኅበረ ቅዱሳን ሻምቡ ማእከል አባል |
| **ነቀምት ከተማ** | | 2 | | 2 | 01 ቀበሌ ፖሊስ ጣቢያ | የምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ዋና ፀሐፊ፣የማኅበረ ቅዱሳን ነቀምቴ ማዕከል አባል |
| **አዲስ አበባ** | | 20 | | 20 | ፉሪ ወረዳ 4 | ከፉሪ መካነ ቅዱሳን አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ እና ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን፣በማኅበረ ቅዱሳን የአራዳ ጉለሌ ወረዳ ማዕከል አባል |
| **ሰበታ** | | 18 | | 18 | | |
| **ወለቴ** | | 5 | 2 | 7 | | ወለቴ ቅዱስ ዮሐንስ አስተዳዳሪው |
| **ኮልፌ/አዲስ አበባ** | | 11 | 3 | 14 | | |
| **ቡሌ ሆራ** | | 1 | | 1 | | |
| **አሰበ ተፈሪ** | | 10 | | 10 | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ያቤሎ** | | 11 | 1 | 12 | | የሰ/ት ቤት ሊቀመንበር፣የያቤሎ ደብረ ፅዮንና እግዚአብሔር አብ ወአቡነሐራ ድንግል ቤ/ክ አስተዳዳሪ፣የቦረና ዮኒቨርሲቲ ተማራዎችና ሰራተኞች |
| **ሻሸመኔ** | | 347 | 97 | 454 | | |
| **ወሊሶ** | | 13 | 0 | 13 | | |
| **መቱ** | | 9 | 0 | 9 | | |
| **ፍቼ** | | 52 | 0 | 52 | | |
| **ቦረና** | | 7 | 0 | 7 | ጊጥሩ ፖሊስ ጣቢያ | |
| **ምዕራብ ሃረርጌ** | | 15 | 0 | 15 | ጭሮ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ | |

## 4. ከሥራ መታገድ፣ መፈናቀል እና ቅጣት

በአዲስ አበባ፣ በምሥራቅ ሐረርጌ፣ በምሥራቅ ሸዋ፣ በምሥራቅ ወለጋ፣ በምዕራብ ወለጋ እና በምዕራብ አርሲ ዞን በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ የነበሩ አገልጋዮች በአዲስ ተሿሚዎች እና በደጋፊዎቻቸው ከሥራ ተፈናቅለዋል። በተለይም ምዕራብ ወለጋ እና ምሥራቅ ወለጋ ተሿሚዎች ከሀገረ ስብከት እስከ አጥቢያ ድረስ ያሉ አገልጋዮችን በማፈናቀል የራሳቸው ደጋፊ የሆኑትን ሹመዋል። በተጠቀሱት አህጉረ ስብከት እንደልብ በሁሉም አካባቢዎች ተንቀሳቅሶ መረጃዎችን መሰብሰብ የሚቻልበት ዕድል ባለመኖሩ አጠቃላይ ከሥራ የተፈናቀሉ አገልጋዮችን ቁጥር ለማወቅ አልተቻለም። ምዕራብ ሐረርጌ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሆኜ ተመድቤያለሁ የሚለው “ቄስ ታደሰ ደርቤ” የሀገረ ስብከቱን ማኅተም በመጠቀም የራሱን ሰዎች እየሾመ እንደበረ ከተላከው መረጃ ማየት ተችሏል። ምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከትና ምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ጥቁር ለብሳችኋል በሚል በመንግሥት ሥራ ላይ የነበሩ ኦርቶዶክሳውያን ከሥራ ታግደው ቆይተው ደመወዝ የተቆረጠባቸውና ከኃላፊነታቸው ዝቅ የተደረጉ ኦርቶዶክሳውያን እንዳሉ ከተላኩት ማስረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል። ምሥራቅ ሐረርጌ ላይ ከሥራቸው ታግደው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸውና የደመወዝ ቅጣት የተላለፈባቸው የተጻፉ ደብዳቤዎች በአባሪ አምስት ስር ተያይዘዋል።

በተጨማሪም በትክክል ተመዝግበው የደረሱንን መረጃዎች በአካባቢው ካሉን የመረጃ ምንጮች ጋር በማገናዘብ ሕገ ወጡን ሹመት ትቃወማላችሁ በሚልና በቅዱስ ሲኖዶስ አዋጅ መሰረት በጾመ ነነዌ ጥቁር ለብሳችሁ ተገኝታችኋል በሚል ምክንያት ከስራ የተባረሩ ግለሰቦች ዝርዝር ከታች ባለው ሰንጠረዥ ላይ ተቀምጧል።

## *ሰንጠረዥ 4፡ ሕገ ወጡን ሹመት ትቃወማላችሁ በሚልና በቅዱስ ሲኖዶስ አዋጅ መሰረት በጾመ ነነዌ ጥቁር ለብሳችሁ ተገኝታችኋል በሚል ምክንያት ከሥራ የተባረሩ ግለሰቦች ዝርዝር*

| የግለሰቡ ስም | ይሰሩበት የነበረ መስሪያ ቤት | የተባረሩበት/የታገዱበት ምክንያት | አሁን ያሉበት ሁኔታ |
|---|---|---|---|
| አቶ ያባብላል ተስፋ | ቦሌ ክፍለ ከተማ ንግድ ፅ/ቤት የንግድ ቢሮ ባለሙያ | የተሰጠው ምክንያት የሀይማኖት ፀብ ለማስነሳት እና ሁከት እና ብጥብጥ አስነስተሀል አሁን ላይ ከስራ ታግዶ ጉዳዩ በዲስፒሊን ኮሚቴ እየታየ ነው። | አይታወቅም |
| ቄስስ እዝራ አበበ | በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረስብከት አመያ ወረዳ ማርያም ቤተክርስቲያን  አስተዳዳሪ | የተወገዙትን አባቶች ስም በቅዳሴ አልጠራህም እና ህገ ወጡን ሢመት ባለመቀበል ከህዝብ ጋር ተቃውመሀል በመባል ከስራ የተሰናበቱት። | አይታወቅም |
| ዲ/ን ፈለቀ አበባ | በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረስብከት አመያ ወረዳ ማርያም ቤተክርስቲያን  የቅጥረኛ አገልጋይ | ተወግዘው ከተለዩት ጋር አልተባበርም በማለታቸው። | አይታወቅም |
| ዲ/ን ንጉሴ ላተራ | በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረስብከት አመያ ወረዳ ማርያም ቤተክርስቲያን  የቅጥር አገልጋይ | ተወግዘው ከተለዩት ጋር አልተባበርም በማለታቸው | አይታወቅም |
| ዲ/ን ፈቃዱ ደጀኔ | በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረስብከት አመያ ወረዳ ማርያም ቤተክርስቲያን የቅጥር አገልጋይ | ተወግዘው ከተለዩት ጋር አልተባበርም በማለታቸው | አይታወቅም |
| ዲ/ን አዳነ ደመቀ | በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረስብከት አመያ ወረዳ ማርያም ቤተክርስቲያን የቅጥር አገልጋይ | ተወግዘው ከተለዩት ጋር አልተባበርም በማለታቸው | አይታወቅም |
| መ/ገ ቆሞስ አባ ወ/ገብርኤል አበበ | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ስራ አስኪያጅ | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው  አንቀበልም በማለታቸው ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | አይታወቅም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሊቀ ት/ ቢንያም ፀጋዬ | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ፀሀፊ | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው አንቀበልም በማለታቸው ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | አይታወቅም |
| መጋቤ ሥርዐት አባ አጋ ቦኩረ | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ህግ ክፍል | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው አንቀበልም በማለታቸው ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | አይታወቅም |
| መ/ሄራን መሀሪ በቃሉ | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት የካህናት አስተዳደር ሀላፊ | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው አንቀበልም በማለታቸው ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | አይታወቅም |
| መ/ሀይማኖት መ/ፅድቅ ታደሰ | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ሰበካ ጉባዔ ማደራጃ ሀላፊ | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው አንቀበልም በማለታቸው ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | አይታወቅም |
| መ/ምህረት ቄስ ግዛቱ ይስማው | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት መዝገብ ቤት | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው አንቀበልም በማለታቸው ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | አይታወቅም |
| ዲ/ን ያሬድ ፍሰሀ | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሹፌር | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው አንቀበልም በማለታቸው ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | አይታወቅም |
| ዲ/ን ለማ ፈንታሁን | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ሂሳብ እና ግዢ ሀላፊ | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው አንቀበልም በማለታቸው ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | አይታወቅም |
| አባ ወልደ ጊዮርግስ ተርሳስ | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት የቦቼ ቅድስት ኪዳነ ምህረት ቤ/ክ | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው አንቀበልም በማለታቸው | አይታወቅም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | አስተዳዳሪ | ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | |
| ቀሲስ ጫነ መንበሩ | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት የሥሬ አማነኤ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የቤተሰብ  አስተዳዳሪ | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው  አንቀበልም በማለታቸው ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | አይታወቅም |
| ቀሲስ ዋቁማ ኤብዮ | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት የሥሬ ሚካኤል ቤተ ክርስትያን አስተዳደር የቤተሰብ አስተዳደሪ | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው  አንቀበልም በማለታቸው ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | አይታወቅም |
| መ/ብረሃናት አባ ወልደ ገብርኤል በቀለ | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት የቅዱስ ገብርኤል ቤ/ክ አስተዳዳሪ | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው  አንቀበልም በማለታቸው ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | አይታወቅም |
| ቄስ አምሳሉ ዘውዱ | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት የጂማ አርጆ ወረዳ ቤተ ክህነት ሀላፊ የቤተሰብ አስተዳዳሪ | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው  አንቀበልም በማለታቸው ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | አይታወቅም |
| መ/ሀይል አባ ህሩየ ስላሴ | የምስራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት የነቀምት ርዕሰ አድባራት ማርያም ቤ/ክ አስተዳዳሪ | ከመንግስት አካል እና ከህገ ወጡ ቡድን በቃል እና በስልክ ተቀበሉ ተብለው  አንቀበልም በማለታቸው ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው | አይታወቅም |
| ሊቀ ሊሳናት ቄስ ወንድወሰን ጥላሁን | የምእራብ አርሲ ሀ/ስብከት ፀሀፊ | | ከስራ ገበታ ከመታገታቸው በተጨማሪ ለእስር የተዳረጉ |
| መ/ር ሰሎሞን ዘገዬ ተጠሪ | የምእራብ አርሲ ሀ/ስብከት ግንኙነት ክፍል | | ከስራ ገበታ ከመታገታቸው በተጨማሪ ለእስር የተዳረጉ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወ/ሮ ሙሉ አያሌው | ፕላን እና ልማት ኮሚሽን | ጥቁር በመልበስ ታግዳ ጉዳዩ በዲስፒልን ኮሚቴ እየታየ ነው። | ተባረው ቆይተው ከሁለት ወር በላይ አግዶ መቆየት ስለማይቻል ወደ ስራ ገበታቸው የተመለሱ |
| ወ/ሮ የትናየት ተሾመ | ፕላንና ልማት ኮሚሽን ፕላን እና ልማት ኮሚሽን | ጥቁር በመልበስ ታግዳ ጉዳዩ በዲስፒልን ኮሚቴ እየታየ ነው። | ተባረው ቆይተው ከሁለት ወር በላይ አግዶ መቆየት ስለማይቻል ወደ ስራ ገበታቸው የተመለሱ |
| ወ/ሮ በለጡ ዘለቀ | ቂርቆስ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር | ጥቁር በመልበስ ታግዳ ጉዳዩ በዲስፒልን ኮሚቴ እየታየ ነው። | ተባረው ቆይተው ከሁለት ወር በላይ አግዶ መቆየት ስለማይቻል ወደ ስራ ገበታቸው የተመለሱ |

## 5. ከቦታ ቦታ ተዘዋወሮ የማገለገል መብትን መገደብ

ሕገወጡ ሹመት ከተፈጸመ በኋላ በነበሩት ተከታታይ ቀናት በቤተ ክስርቲያን በተለያየ ሃላፊነት የሚያገለግሎ ከብጹዓን አባቶች ጀምሮ በተዋረድ ያሉ አገልጋዮች ለተለያየ ተልእኮ በተለይም በኦሮሚያ ክልል እንዳይጓዙ፤ ተጉዘውም የነበሩ በመንግስት የጸጥታ አካላት ተገደው እንዲመለሱ ተደርገዋል። ለአብነት ያክል

1. ጥር 20 2015 ዓ/ም ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ (ዶ/ር) ፣ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ፣ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ፣ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል፣ ንቡረእድ ኤልያስ አብርሃ፣ ሊቀ አእላፍ ቀሲስ በላይ መኮንን፣ ሊቀ ማእምራን ፋንታሁን ሙጬ እና ሊቀ ትጉኃን እስክንድር ገብረ ክርስቶስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ለመመረቅ ወደ ጅማ ሀገረ ስብከት እንዳይሔዱ ተከልክለው ከቦሌ አየር ማረፊያ ተመልሰዋል።
2. ጥር 20 2015 ዓ/ም ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ እና ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ ወደ ጅማ ሀገረ ስብከት እንዳይገቡ ከጅማ አየር ማረፊያ እንዲመለሱ ተደርጓል።
3. ጥር 30 2015 ዓ/ም ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል ወደ ሀገረ ስብከታቸው ለመሔድ ጅማ አየር ማረፊያ ሲደርሱ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ ተደርገዋል።
4. ጥር 26 ቀን 2015 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ያሬድ ከሀገረ ስብከታቸው (አርሲ) ከምሽቱ 3፡30 በጸጥታ ኃይሎች ተወስደው 5፡20 ላይ በሌሊት ተገድደው ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ ተደርገዋል።

5. ብፁዕ አቡነ እንጦንስ ወደ ሀገረ ስብከታቸው ምዕራብ ሐረርጌ እንዳይገቡ ተከልክለዋል።

በተለይም ወለጋ አካበቢ አዲስ ተሿሚዎች በቆዩባቸው ጊዜያት ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን አይሔዱም። ቅዳሴና ቅዱስ ቁርባን የለም ከሚባልበት ደረጃ ደርሷል። በትንሣኤ በዓል ዕለት ምእመኑ ሌሊት ሄዶ ቤተ ክርስቲያን ተሳልሞ ከመመለስ ውጪ አዳር አልነበረም፤ ቅዱስ ቁርባን የተቀበለ የለም። አገልግሎቱ በከፍተኛ ሁኔታ ተስተጓጉሎ እንደነበርና ምእመናን ከቤተ ክርስቲያን ለመራቅ ተገደው እንደነበር ለማወቅ ተችሏል።

## 6. የግለሰቦችና የተቋማት ንብረት መውደም

አዲስ ተሿሚዎች የገቡባቸው ቄለም ወለጋ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና፣ ሆሮጉዱሩ ወለጋ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና፣ ምዕራብ ወለጋ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና፣ ምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና፣ ምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና፣ አርሲ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና እና ምዕራብ አርሲ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና ተሰብረው ተይዘዋል። የመናብርተ ጵጵስና ቢሮዎች ተገንጥለዋል። አሰበ ተፈሪ ቅድስት ልደታ ቤተ ክርስቲያን፣ ሻሸመኔ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን እና ወለቴ ቅዱስ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ጉዳት የደረሰባቸው አጥቢያዎች ናቸው።

ሻሸመኔ ደብረ ስብሐት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ቤተ ክርስቲያኑን ለመጠበቅ የገባውን አገልጋይና ምእመን ገድለው ደብድበው ካስወጡ በኋላ ሙሉ ለሙሉ ግቢውን በመቆጣጠር፣ ክፍሎችን በመሰባበር፣ ሙዳየ ምጽዋትን በመመዝበር ከፍተኛ ዝርፊያ ፈጽመዋል፡፡ ቤተ መቅደሱን ሰብሮ በመግባት መንበሩን በመስበር የቃል ኪዳኑን ታቦት አስከመዳፈር ደርሰዋል። በመኪና ተጭነው መጥተው በያዙት ሁሉ ሕዝበ ክርስቲያኑን ሲያጠቁ የነበሩት ወጣቶች ከነጫማቸው ወደ ቤተ መቅደስ በመግባት በቤተ ክርስቲያን ላይ የቀለዱበት ትዕይንት ትልቅ የታሪክ ጠባሳ ነው፡፡ መሣሪያ ተደብቋል በሚል መካነ መቃብር በመክፈት አስከሬኑን በማውጣት ሜዳ ላይ ጥለው የወጡበት አግባብም ነበር። የሀገረ ስብከቱን ጽ/ቤት ከሰበሩ በኋላ የመምሪያ ኃላፊዎችን በማሰር ጽ/ቤቱን በመመዝበር ከፍተኛ ወንጀል ፈፅመዋል፡፡ መልስ ሰጪዎች ስለ አጠቃላይ ሁነቱ ሲገልጹ "በቋንቋው አልተማረም ብለው ወዳዘኑለት ሕዝብ ለማስተማር የመጡ ሳይሆን የጠላት አገር በወረራ የያዙ ይመስል ነበር" ብለዋል። ለምሳሌ ምሥራቅ ወለጋ መንበረ ጵጵስናውን ከሰበሩ በኋላ የሀገረ ስብከቱን ሊቀ ጳጳስ ንብረት ዘርፈዋል። የሀገረ ስብከቱን የንዋየተ ቅድሳት ካዝና በመሰባበር የሚፈልጉትን ከዘረፉ በኋላ ተቃውሞ እንዳይነሣባቸው በሌሊት ወደ ጋራዥ ወስደው አስጠግነውታል።

# በሕገ ወጥ ሹመቱ ተሳታፊ የነበሩ አካላት

የቅዱስ ሲኖዶስ ፍጹም አንድነት፣ ቅዱስ ፓትርያርኩ፣ ብፁዕ ዋና ሥራ አስኪያጁና የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ጽኑዕና የተናበበ አካሔድ፣ የኢመደበኛ ሚዲያው ግሩም አፀፋ፣ የኪነ ጥበብ ሰዎች ተቆርቋሪነት፣ የሌላ ቤተ እምነት ሰዎች አጋርነት፣ የአኃት አብያተ ክርስቲያናት ድጋፍ፣ ካቶሊካውያንና የምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን መሪዎች የሰጡት ምላሽ፣ ከሁሉም በላይ አዲስ ተሿሚዎች የተመደቡባቸው አህጉረ ሰብከት ምእመናንና ካህናት ሕይወትን እስከ መስጠት የደረሰ ሰማዕትነትና ጥብዓት በእርግጥም የቤተ ክርስቲያን ማኅፀን እንደማይነጥፍ ማሳያ ነው፡፡ የአማራ ክልልና የደቡብ ምዕራብ ክልል ያወጡት መግለጫም በአዎንታዊነት የሚጠቀስና የቤተ ክርስቲያንን የአገር ባለውለታነት ያልዘነጋ ነበር። በሌላ በኩል ቀላል የማይባል

ኃይል የቤተ ክርስቲያንን መብትና ጥቅም በመጻረር ተሳትፏል፡፡ ተሳታፊዎች የሰጡት መልስ የእነዚህን አካላት ማንነት መለየትንም ያካትታል፡፡ በዚህ አንጻር ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ በየሀገረ ስብከቱ የእንቅስቃሴው መሪ ተዋናይ እና ደጋፊ ናቸው ተብለው የተለዩት አካላት ጠቅለል ባለ መልኩ የሚከተሉት ናቸው። ድጋፋቸውን በተመለከተ ከሃሳብ ጀምሮ በገንዘብ፣ በጉልበት፣ በሙያና በሥልጣን እስከ መደገፍ እንደሚደርስ ተገልጿል።

## 1. የፌደራል መንግሥት

የፌደራሉ መንግሥት ከዚህ በፊትም በነበረው ቁመና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትን ለማናገር ፈቃደኛ ካለመሆን ጀምሮ፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚፈጸሙ በደሎችንና ችግሮችን ያለመቀበል ችግር ይታይበት ነበር። ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በብዙ ልመናና ውትወታ ጳጉሜን 1 ቀን 2011 ዓ.ም ውይይት ለማድረግ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሔዱበት ወቅት በቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሰ ያለው በደልና ግፍ ይቁም የሚለውን የአባቶችን ተማጽኖ፡-

*"ይህ አቤቱታ ሳይሆን ክስ ነው፤ እንዴት ወርቅ ላበደረ ጠጠር እባላለሁ? እንዲህ ዐይነቱን ክስ ለአቶ መለስና ለአቶ ኃይለ ማርያም አቅርባችሁ ታውቃላችሁ? እስካሁን እንዲህ የጳፋችሁባቸው መሪዎች የሉም። ካሉም አያይዛችሁ አቅርቡ ... እኔ ቤተ ክርስቲያንን ስላላቃጠልሁ ካሣ አልከፍልም፤ እኔ ምእመናንን ስላላገደልሁ ካሣ አልከፍልም፤ እኔ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ስላልበደልሁ ይቅርታ አልጠይቅም፣ ይቅርታ የሚጠይቀው ንስሐ የሚገባው የበደለ ሰው ነው፤ እኔ ደግሞ አልበደልሁም። ... እዚህ ውስጥ በካድሬ ያልተሾመ ማን አለ? ደኅንነቶቼን ልኬም እርምጃ መውሰድ አላቃተኝም ..."* የሚል ረጅም ሐተታና ማስፈራሪያ ነበር ያስተላለፉት። [11]

ጥር 15 2015 ዓ/ም በተፈጸመው ሕገ ወጥ ሹመት መንግሥት አስቀድሞ ስለ ጉዳዩ እያወቀ በዝምታ ከማለፍ ጀምሮ፣ ድርጊቱ ከተፈጸመም በኋላ ሕጋዊ ሰውነት ያላትን ቤተ ክርስቲያንን ከመጠበቅ ይልቅ ሕጋዊ ላልሆነ አካል ከለላ የመስጠት ሥራ ሲሠራ ነበር። ጥር 23 ቀን 2015 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ካቢኔዎቻቸውን ሰብስበው "ማንም እጁን እንዳያስገባ" በማለት ያስተላለፉት ማስፈራሪያ፣ ጉዳዩን የሃይማኖት ሳይሆን የፖለቲካ ቅርፅ በመስጠት በዓላማ እየተሠራበት እንደሆነ ማሳያ ነው። ከዚያ በኋላም ጥር 28 ቀን 2015 ዓ.ም በመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት የተሰጠው መግለጫ ቤተ ክርስቲያንን ከአዲስ ተሿሚዎች ያነሰ ዕውቅና ያላት በማስመሰል ያቀረበ ነበር። ቤተ ክርስቲያን መንግሥት ለጥያቄዋ መልስ የማይሰጣት ከሆነ ዓለም አቀፍ ሰልፍ እንደምታደርግ ባሳወቀች ጊዜም [12] የካቲት 4 ቀን 2015 ዓ.ም በጸጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይሉ በኩል ቤተ ክርስቲያን የጠራችውን ሰላማዊ ሰልፍ በአሸባሪ አካላት የተጠራ ሰልፍ በማስመሰል የተሰጠው መግለጫ ተንኳሽ፣ ገፊና አሸማቃቂ ነበር። መንግሥት ይህን ሁሉ በደል ከፈጸመ በኋላ ራሳቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሸማጋይ ሆነው የቀረቡበት አግባብ መንግሥት የጉዳዩ መሪ ተዋናይ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ቤተ ክርስቲያን ልጆቿ የነነዌን ጾም ጥቁር ልብስ በመልበስ እንዲያሳልፉ ባወጀችበት ወቅት ለክልሎች ምንም እንቅስቃሴ እንዳይደረግ ትእዛዝ በመስጠት፣ የፌደራሉ መንግሥት መቀመጫ በሆነችው አዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ አካባቢዎች ምእመናንን ከቤት ጥቁር ልብስ ለብሰው እንዳይወጡ የሚከለክሉ ፖሊሶችን በመመደብ፣ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ ቆመው ጥቁር ለብሰው እንዳይገቡ በመከልከል፣ ጥቁር ለብሰው የተገኙ ምእመናንን ከቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ ሳይቀር አፍሶ በመውሰድ በማሠር፣ የቤተ ክርስቲያን ጥበቃዎችን ለጥበቃ የተፈቀደና የተመዘገበ መሣሪያ በመውሰድ፣ የካቲት 5 ቀን 2015 ዓ.ም ምእመናን በአጥቢያቸው ተገኝተው ቅዳሴ እንዳያስቀድሱ ከስድስት ኪሎ እስከ መስቀል ዐደባባይ፣ ከመስቀል ዐደባባይ እስከ ልደታ መንገድ

በመዝጋት ከሌሊቱ 11:00 ጀምሮ ወታደራዊ ትርዒት ማሳየት፣ ጥቁር ልብስ ለብሰው ወደ ቢሮ የሔዱ ሠራተኞችን እንዳይገቡ በመከልከል፣ ከሥራ በማገድና በማሰናበት፣ ጥቁር ልብስ የለበሱ ባለጉዳዮችን አገልግሎት እንዳያገኙ በመከልከል፣ ብዙ ኦርቶዶክሳውያንን በገፍ በማሠርና በማንገላታት፣ በሕግ ዋስትና የተፈቀደላቸውን ያለ ሕግ የፍርድ ቤት ትእዛዝን ባለማክበር በእስር እንዲቆዩ በማድረግ፣ ወዘተ ብዙ ተንኳሽና ሕዝበ ክርስቲያኑን ለቁጣ የሚያነሣሡ ድርጊቶች ተፈጽመዋል።

እነዚህ ሁሉ ድርጊቶች መንግሥት የሿሚዎችንና የተሿሚዎችን እንቅስቃሴ እንደሚደግፍ ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያን መብቷን ለማስከበር የምትወስዳቸውን ሰላማዊ አካሔዶች ወደ አመጽ ለመቀየር ይሠራ እንደነበር ነው። ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን አገራዊ ውለታ የረሳ፣ ቤተ ክርስቲያንን የመከፋፈልና የማዳከም ግልጽ ተልእኮ ነው። በተጨማሪም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት የሚመራው የፀጥታና ደህንነት የጋር ግብረ ሃይል የካቲት 1 2015 ዓ/ም ባወጣው መግለጫ [13] ቤተ ክስርቲያኗ የካቲት 5 2015 ዓ/ም የጠራችውን ሰላማዊ ሰልፍ "ሕገ ወጥ ሰልፍ" በማለት የጠራው ሲሆን በሃይማኖት ሽፋን የሚደረግ የሽብር ተግባር ስለሆነ ሰልፉን በሚያስተባብሩና በሚያደርጉ ላይ እርምጃ መንግስት ይወስዳል በማለት ከአንድ ሃገርን ከሚመራ መንግስት በማይጠበቅ መልኩ የቤተ ክርስቲያን አባቶችንና ምእመናንን የሽብርተኝነት ታርጋ እስከመለጠፍ ደርሷል።

## 2. የኦሮሚያ ክልል መንግሥት

የክልሉ መንግሥት ቤተ ክርስቲያን በሿሚዎችና በተሿሚዎች ላይ ያስተላለፈችውን ውግዘት በመኮነን "የቁም ቀር አስተሳሰብ" እንደሆነ ያወጣው መግለጫተሿሚዎቹ ወደተለያዩ አህጉረ ስብከት ሔደው ሪፎርም ላይ ስለሆንን ከለውጡ ጋር የሚስማማ ይቀጥላል፤ የማይስማማ ይወጣል ካሉት ጋር የሚስማማ ነው። የሹመት ቦታውን ከመምረጥ ጀምሮ፣ ቦታውን በጸጥታ አካላት በማስጠበቅ፣ ለተሿሚዎች ማረፊያ ቦታ በማዘጋጀት፣ አስፈልጊውን ግብዓት በማሟላት በአጠቃላይ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ጉዳዩን በበላይነት በመምራትና ለተሿሚዎቹ ሕጋዊ ጥበቃና ከለላ በመስጠት ድጋፉን አሳይቷል።

ለአዲስ ተሿሚዎች ከሹመቱ ዕለት ጀምሮ ጠባቂዎችን መድቧል፤ የሕግ ባለሙያዎችን አደራጅቶ ጥብቅና እንዲቆምላቸው አድርጓል፤ በጸጥታ አካላት አጀብ የአህጉረ ስብከትን መንበረ ጵጵስና ሰብረው እንዲገቡ አድርጓል። ቤተ ክርስቲያናቸውን ለመጠበቅ የወጡ ኦርቶዶክሳውያንን ገድሏል፤ አስሯል፤ አንገላቷል። የክልሉ መንግሥት በአቋም አዲስ ሲኖዶስ እንዲቋቋም እየሠራ ነበር። በዚህ እንቅስቃሴ ለደረሰው ጉዳትም ሆነ፣ ለእነዚህ አካላት እንደ ልባቸው መሆን የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ነው። በተጨማሪም በክልሉ ባሉ ዞኖችና ወረዳዎች ለተሿሚዎች ድጋፍና አቀባበል በማድረግ፣ ሕዝቡን በግድ ወጥቶ እንዲቀበል በመቀስቀስ፣ ያልወጣውን ምእመን በማስፈራራት፣ እንቅስቃሴውን ይቃወማሉ ብለው የሚያስቧቸውን አካላት ሰላይ በመመደብ መውጫ መግቢያ በማሳጣት፣ ያለምንም ጥፋታቸው ኦርቶዶክሳውንን በማፈን፣ በማሰርና በማንገላታት፣ ከሥራ ቦታ እንዲባረሩ በማድረግ፣ አካባቢውን ለቀው ካልወጡ ርምጃ እንደሚወሰድባቸው በመዛትና በማሸማቀቅ፣ የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት በአዲስ ተሿሚዎችና በደጋፊዎቻቸው እንዲዘረፍ በማድረግና መንበረ ጵጵስናዎች በህገ ወጥ አካላት እንዲሰበሩና እንዲዘረፉ በማድረግ ተሳትፎ ነበራቸው።

## 3. የግል ተቋማትና ግለሰቦች

ተጠሪነታቸው ለፌደራል መንግስት ከሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ ፣ ጅማ ዩንቨርስቲ ፣ ቦንጋ ዩንቨርስቲ ፣ አምቦ ዩኒቨርስቲ፣ ሃሮምያ ዩኒቨርሲቲና የኢትዮጲያ ቴክኒካል ዩንቨርሲቲ በቅዱስ ሲኖዲስ ጥቁር በመልበስ የነነዌ ጾምን በሱባኤ ምእመናን እንዲያሳልፍ የታዘዘውን መሰረት በማድረግ ጥቁር የለበሱ ተማሪዎችንና ሠራተኞቸን በመደብደብና ወደ ግቢ እንዳይገቡ በመከልከል ከፍተኛ በደል እንደፈጸሙ በወቅቱ ጉዳት የደረሰባቸው ሠራተኞችና ተማሪዎች ገልጸዋል።

በተጨማሪም ሕገወጥ ሹመቱን የሚደግፉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ለዚህ እንቅስቃሴ ብዙ ገንዘብ የሰጡ ሲሆን የሆቴል ኪራይ፣ የሹመት አልባሳት፣ የትራንስፖርትና የምግብ ወጪ በመሸፈን ድጋፍ ያደረጉ ባለሀብቶችም አሉ። በአብዛሃኛው እነዚህ ባለሃብቶች በሃይማኖታቸው የሌላ ቤተ እምነት ተከታዮች መሆናቸው የድጋፉ ምክንያት ምን እንደሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ ያደርገዋል። ከነዚህም ባለሃብቶች መካከል ሁንዴ ሁጋሳ የጀንቦ ስታር ግሩፕ ሥራ አስፈጻሚ፣ ግሬት ላንድ ሞተር ኤንድ አኒንጂነሪንግ ኀ/የተ/የግ/ማኀ፣ ጥላሁን ጫላ አስመጪና ላኪ፣ ኤቢኤች ፓርትነር፣ ሊድ ስታር ሚኒስትሪ፣ ዜኒት በሽር፣ በያን ኢብሮ አብደላ፣ ፓስተር አብዱ ጂሬኛ፣ ኡስማን አብዱል ሰላም፣ ፓስተር ገመቺስ፣ ነጋሺ ከድር፣ ሊዲያ ማሞ፣ ዳዴ ሐጂ በራርቲ፣ ሡልጣን አባጌሳ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። አባ ሳዊሮስ እና አባ ዜና ማርቆስ በእጃቸው ተቀብለው ገቢ ያደረጉትን ጨምሮ በአባ ሳዊሮስ የአዋሽ ባንክ ሒሳብ ቁጥር ከጥር 22-25 ቀን 2015 ዓ.ም ገቢ የተደረገ ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ እንደተገኘ መረጃዎች ያሳያሉ። ድጋፍ ያደረጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች እና ያደረጉት የድጋፍ መጠን በሚከተለው ሰንጠረዥ ተቀምጧል።

ሰንጠረዥ 5፡ ለሕገ ወጡ ሹመት ድጋፍ ያደረጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች እና ያደረጉት የድጋፍ መጠን

| ተ.ቁ. | የድጋፍ አድራጊው ስም | ያደረገው የድጋፍ መጠን | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | በያን ኤብሮ አብደላ | 2,000,000.00 | ሙስሊም |
| 2 | ገመቺስ ፈቀደ ሶሪ | 2,000,000.00 | ፕሮቴስታንት |
| 3 | አብዲ ተስፋዬ ጂሬኛ | 2,000,000.00 | ፕሮቴስታንት |
| 4 | ዜኒት አሰፋ በሽር | 2,000,000.00 | ሙስሊም |
| 5 | አባ ሳዊሮስ ሞጎር | 2,050,000.00 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 6 | ውዳሴ ፋላስ በርዋቅ | 1,000,000.00 | |
| 7 | አበባየሁ አበበ ታደሰ | 1,000,000.00 | |
| 8 | አባ ዜና ማርቆስ | 1,000,000.00 | |
| 9 | ብሩ በቀለ ዋቅጅራ | 1,000,000.00 | |
| 10 | ፈቃዱ ከበደ ፈዬ | 1,000,000.00 | |
| 11 | ኡስማን አብዱሰላም ሼክ ኡስማን | 1,000,000.00 | ሙስሊም |
| 12 | ኩራዝ መኮንን ፋፋ | 950,000.00 | |
| 13 | ማቲ ፈቃዱ ደበላ | 500,000.00 | |
| 14 | ሊዲያ ማሞ እሸቴ | 500,000.00 | ፕሮቴስታንት |
| 15 | ግሬት ላንድ ሞተርና ኢንጂነሪንግ | 500,000.00 | |
| 16 | አያና ገለታ በየነ | 500,000.00 | |
| 17 | ጃምቦ ስታር ትሬዲንግ ኀ.የተ.የግ.ማ | 500,000.00 | |
| 18 | ኤቢኤች ፓርትነር | 300,000.00 | |
| 19 | ዳዲ ሐጂ በራርቲ | 250,000.00 | ሙስሊም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 20 | ቡልቡላ ጡሌ ዴከቦ | 150,000.00 | |
| 21 | ነጋሽ ሸቆ ከድር | 100,000.00 | ሙስሊም |
| 22 | ጥላሁን ጫላ አስመጪና ላኪ | 100,000.00 | |
| | ድምር | 20,400,000.00 | |

## 4. ሌሎች ቤተ እምነቶች

ምሥራቅ፣ ምዕራብና ሆሮጉዱሩ ወለጋ በአብዛኛው ፕሮቴስታንቶች እና አንዳንድ ሙስሊሞች፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ ደግሞ ሙስሊሞች ለአዲስ ተሿሚዎች ድጋፍ ሲያደርጉ ነበር። በተለይም ምዐራብ አርሲ ተመድበዋል የተባሉት አዲስ ተሿሚ ከሙስሊሞች ጋር ስብሰባ ተቀምጠው ሲመካከሩና በሬ ተገዝቶ ሲሰጣቸው እንደነበር ከመልስ ሰጪዎች የመጡት መልሶች ያስረዳሉ። ከተለያዩ አካባቢዎች በመኪና ተጭነው አባቶቻችንን ልንቀበል ነው ብለው ይመጡ የነበሩት ወጣቶች በአብዛኛው ምንም ዐይነት እምነት የሌላቸው እና የሌሎች ቤተ እምነቶች ተከታዮች እንደሆኑ ተገልጿል። በአባ ሳዊሮስ የሂሳብ ቁጥር ለእንቅስቃሴው ድጋፍ ገንዘብ ገቢ ካደረጉት አካላት ውስጥ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች እና ሙስሊሞች ይገኙባቸዋል።

## 5. ሚዲያዎች

ኦሮሚያ ሚዲያ ኔትወርክ፣ ኦሮሚያ ብሮድካስት ሰርቪስ፣ ኩሽ ሚዲያ፣ ፕራይም ሚዲያ፣ የእኛ ቲቪ ሌሎችም ማኅበራዊ ሚዲያዎች የእነዚህን አካላት እንቅስቃሴ አግባብነት ሽፋን በመስጠት ከፍተኛ ሚና ነበራቸው። እነዚህ ሚዲያዎች የአዲስ ተሿሚዎች የቴሌቪዥን ጣቢያ እስከሚመስሉ ድረስ በወቅቱ ሰፊ ሽፋን ይሰጡ ነበር። የመንግሥት ሚዲያዎች (ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት፣ ዋልታ፣ ኢቢሲ እና አዲስ ሚዲያ ኔትወርክ) በ2012 ዓ.ም የተጀመረውን የኦሮሚያ ቤተ ክህነት እንቅስቃሴ ስለ ችግሩ መፈጠር ሳይናገሩ ቆተው ጉዳዩ በእርቅ ተፈታ የሚለውን ብቻ እንደዘገቡት አሁንም በተመሳሳይ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ተደረገ የተባለውን ውይይት ከማስተላለፍ ውጪ ከዚያ በፊት ስለ ጉዳዩ ምንም ዐይነት ዘገባ ባለመሥራት ነፃና ገለልተኛ ሚዲያ አለመሆናቸውን አሳይተዋል። ይህን አድራጎታቸውንም የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኀን ባለሙያዎች ማኅበር አግባብነት እንደሌለው በመግለጽ መግለጫ አውጥቷል [8]። ኢቢኤስ ቴሌቪዥን ደግሞ ጉዳዩ በስምምነት ተጠናቀቀ እስከተባለበት ዕለት ድረስ ለጉዳዩ ምንም ዐይነት ሽፋን ሳይሰጥ ቆይቶ በመጨረሻው ዕለት ጉዳዩ በዕርቅ እንደተፈታ በመጥቀስ በዜና መልክ በመዘገብ አልፎታል። እነዚህ ሚዲያዎች ከዚህ በፊትም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚፈጸሙ በደሎችን፣ ሳዘግቡ ያለፉ መሆኑ ይታወቃል።

## 6. ማኅበራት

በተለያዩ አካባቢዎች የተቋቋሙ አንዳንድ አገልግሎት ማኅበራት የዚህ እንቅስቃሴ ፊታውራሪ ሆነው ታይተዋል። ወልዳ ዱካ ቦታ (ማኅበረ ሐዋርያት) እና ወልዳ ዳንዲ ቂልቂሎታ (ማኅበረ ፍኖተ ቅዱሳን) ይህን እንቅስቃሴ አስቀድሞ እውን እንዲሆን ሲሠሩ፣ አሁንም በብርቱ ሲደግፉ እንደነበር ተገልጿል። ድጋፋቸውን በተመለከተ ጥናቶችን በማጥናት፣ ተሿሚዎችን በመመልመል፣ የአቀባበል መርሐ ግብር በማዘጋጀት፣ ወዘተ ነው።

# ማጠቃለያ

ከላይ በመነሻው ላይ ለማስቀመጥ እንደተሞከረው የዚህ ሪፖርት ዋና ዓላም በጥር 14 2015 ዓ/ም ከተፈጸመው ሕገ ወጥ የጳጳሳት ሹመት ጋርና ከሹመቱ በኋላ በተከሰቱ ችግሮች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ በሆኑ አገልጋዮችና ምእመናን ላይ የደረሰውን ጉዳት ዘግቦ መያዝ ነው። ምንም እንኳን ችግሩ በቤተ ክስርቲያኗ ስርዓትና በአባቶቹ መካከል በተደረገ ስምምነት [14] መሰረት የተፈታ መሆኑን ቅዱስ ሲኖዶስ ያሳወቀ ቢሆንም በምእመናን ሞት ምክንያት የሆኑ ግለሰቦችና የጸጥታ አካላት ላይ ምንም አይነት ሕጋዊ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣ በተጨማሪም ያለምንም ወንጀልና የፍርድ ቤት ክስ ለወራት በእስር ተይዘው የቆዩና አሁንም ድረስ በእስር ላይ ያሉ ምእመናን ፍትህ ማገኘት የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር ይቻል ዘንድ መረጃዎቹን አሰባስቦ ማስቀመጡ ግድ ይላል።

በዚህ ዘገባ የተካተቱ መረጃዎች በተቻለ መጠን የማረጋገጥ ስራ የተሰራ ሲሆን በአንዳንድ አካባቢዎች እስካሁንም ድረስ በቀጠለው የጸጥታ ችግር ምክንያት የሪፖርቱ አካል መሆን የሚገባቸው ተጨማሪ ማስረጃዎችን በአካልም ይሁን በአካባቢው በሚገኙ የመረጃ ሰዎች ለማሰባሰብ አስቸጋሪ አድርጎታል። ስለሆነም በቀጣይ በሚገኙ ተጨማሪ ማስረጃዎችን በማካተት የማስተካከያ ስራ የሚሰራ ይሆናል።

# አባሪ መረጃዎች

1. በሕገውጥ ኤጲስ ቆጶሳት ከሾሙትና ከተሿሚዎች ሹመቱን አስመልክቶና የተሿሚዎቹን ምደባ በተመለከተ የሰጡት ሙሉ መግለጫ
2. ከኢትዮጵያ ኦርቶደክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ አዋጅ
3. የጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ ሃይማኖታዊ ክህደት ፣ ቀኖናዊ ጥሰት እና አስተዳደራዊ ግድፈት የታየበትን የወሊሶውን “ሹመት” አወገዘ ቅዱስ ሲኖዶስ ተገቢውን ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ምዕመናን በጸሎት እንዲቆዩ አሳሰበ
4. ከኢትዮጵያ ኦርቶደክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ውግዘት ያስተላለፈበት መግለጫ
5. የአኃት አብያተ ክርስቲያናት፣ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ እና የተለያዩ ቤተ እምነቶች የአቋም መግለጫዎች
6. የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን
7. ከሀይማኖት ጋር ተያይዞ ባለው ወቅታዊ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ የተሰጠ መግለጫ
8. ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ማህበር የተሰጠ መግለጫ
9. AEPAC Press Statement on Ethiopian Orthodox Church – የኤፓክ ፕሬስ መግለጫ (Feb. 8, 2023)
10. የፖለቲካ ፓርቲዎች መግለጫ ከኢሕአፓ መኢአድና እናት ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ
11. ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) ለሚኒስትሮችና ለካቢኒ አባላት በሰጡት የወቅታዊ ጉዳይ ማብራሪያ
12. ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅደስ ሲኖዶስ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ወቅታዊ ጉዳይ ከመንግሥት ጋር እየተደረገ ስላለውው ውይይት እና የካቲት ፭ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊደረግ ስለታሰበው ሰላማዊ ሰልፍ አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ
13. ከፀጥታና ደኅነት የጋራ ግብረ–ኃይል ወቅታዊ የጸጥታ ጉዳይን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ
14. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንና ተወግዘው በተለዩት አባቶች መካከል በሽማግሌዎች አማካኝነት የተደረገው ስምምነት ሰነድ።